# የህብረት ትግል ለምን?

**ብርሃኑ ነጋ፣**

*(ግንቦት 7 ቀን 2001 ዓም፣ እስቶክሆልም ስዊድን በግንቦት 7 ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የቀረበ ንግግር)*

ከሁለት ሳምንታት በፊት ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ባደረግሁት ንግግር የኢትዮጵያችንን የወደፊት የፖለቲካ ዕጣ በሚመለከት አራት “የሊሆን ይችላል” ትንተናዎችን አቅርቤ፣ ተመራጩ “ሁለተኛው አማራጭ፣ አስቀድሞ በተዘጋጀና የሚሄድበትን በሚያውቅ የጋራ ትግል ለውጡ ቢመጣ የሚለው ነው” በሚል የግንቦት ሰባትን ርዕይ ለታዳሚው አካፍዬ ነበር። ለዚህም የህብረት ትግል አስፈላጊነትን በተመለከተ ኦፊሴላዊ ጥሪ ከዲሲ መድረክ አድርጌ ነበር። በዛሬው ውይይታችን፣ ይህ ዲሲ ላይ በጥሪ ደረጃ የተወረወረ ሃሳብ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ፣ እስከዛሬስ ለምን ሳይሰምርልን እንደቀረ፣ ካለፉት የህብረት ተሞክሮዎቻችን ምን ልንማር እንደምንችል የሚጠቃቅሱ ጥቂት ጉንተላዎች አደርግና፣ ሃሳቡን በናንተም ተሳትፎ በጋራ እንድናዳብረው እፈልጋለሁ። አሜሪካኖቹ “የታውን ሆል ሚቲንግ” በሚሉት መልክ “የሃገር ወዳዶች ሸንጎ” ተቀምጠን መመካከር ከቻልን ከምዕራባውያኑም በተሻለ፣ ከመሪዎች ዲስኩር ይልቅ፣ የህዝቡ ተስፋና ፍርሃት የሚደመጥበት መድረክ ሊሆን ስለሚችል ሃገራችን ትጠቀማለች ብዬ አስባለሁ።

## <u>የህብረት የትግል መድረክ ለምን ያሻናል?</u>

ሃገራችን ኢትዮጵያ በልዩ ቀለማት ያሸበረቀች ነች። በአስር ሺህ ጫማ ከፍታ ከሚኖሩ ደገኞች እስከ 11 ጫማ ከባህር ወለል በታች እስከሚኖሩ ቆለኞች፣ ከ80 በላይ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ብሂረሰቦች፣ ሶስቱ የአለም ትላልቅ ሃይማኖቶች የሚገኙባት፣ አረብ ከሚመስሉ የወሎ ቆነጃጅት ሌላውን የአፍሪካ ክፍል የሚያስንቁ ሎጋ አኝዋኮች፣ በነዚህ ሁሉ የህዝቦች ህብር የተዋበች ሃገር ናት። ከነዚህ የቀለም፣ የቁመና፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋ ልዩነቶች የሚመነጩ የስነ ልቡና መለያየቶችም እንዳሉን መቀበል ሊያስፈራን አይገባም። ደገኞቹ እህቶቻችንን ለቆለኞቹ አኝዋኮች ለመዳር ደገኞቹ ደስተኛ እስክንሆን ድረስም፣ ቀስ በቀስ እየቀረፍነው የምንሄደው ረጅም ጉዞ ይመስለኛል። የደገኛውም ብቻ ሳይሆን፣ ያቺ ውበቷን ፍንትው ለማድረግ በከንፈሯ ላይ የሸክላ ገል የምታጠልቅ የሃመር ቆንጆ፣ በቀይ ዳማው ጎንደሬ ገፅ ላይ መልከ መልካምነትን እስኪታይ ድረስም አብሮን ያዘግም ይመስለኛል። ስለሆነም፣ የመጀመሪያው ስምምነታችን ሊሆን የሚገባው፣ ኢትዮጵያ የአንድ ህዝብ ሃገር ናት ስንል፣ በቋንቋም በስነ ልቦናም፣ በዘውግም የተለነቆጠች ወይም ታሽታ አንድ የሆነች ሃገር ናት ማለታችን ሳይሆን፣ ይህ ከላይ ያነሳናቸው ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች እንዳሉም ሆነው፣ እነዚህን ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች አልፎ ከበስተወዲያ የዘገንነው፣ በሰብአዊ ክህሎታችን አምጠን የወለድነው አንድነት አለን ማለታችን ብቻ ነው። ይህም አንድነት ከነፃነት ጥማታችን የተወለደ፣ ከዜጋዊ ግዴታችን በውዴታችን ያመጣነው፣ እንደ ህዝብ በጋራ አናስደፍርም ያልነው፣ የሞትንለት የተሰየፍንለት ብርቅዬ ነው። ገብርዬ፣ ባልቻ፣ ሃይለማርያም ማሞ፣ ገረሱ ዱኪና ሌሎችም አርበኞቻችን፣ እምቢ ለእንግሊዝ፣ እምቢ ለጣሊያን፣ እምቢ ለፋሽስት ብለው፣ ደረታቸውን ለወራሪዎች ሰጥተው፣ ለሃገራቸው ጋሻ ሲሆኑ፣ ስለልዩነታቸው እያሰላሰሉ ሳይሆን፣ ሃገራቸው በእቅፏ ለያዘቻቸው ዜጎቿ ሁሉ ጠለላ እንድትሆን፣ ለነፃነቷ ያደረጉት መስዋእትነት ነው።

ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች አሉን፣ ቢሆንም፣ በላቀና ለነፃነት በተከፈለ መስዋእትነት የተፈተለ፣ የተጋመደና የተሸረበ፣ የአንድነት ታሪክ ባለፀጋዎችም ጭምር ነን። ስለሆነም፣ ስለ ህብረት ትግል ስናሰላስል፣ የዛሬውን የቋንቋና የስነ ልቡና ልዩነቶች መኖር፣ እንደ ጋሬጣ ሳይሆን፣ የዚህችን ታሪካዊት ሃገር ቀጣይነት እንደሚያጠብቅ የማሪያም መቀነት ልናየው ይገባል እላለሁ። የህብረት ትግል አንዱ ዋነኛ ምክንያት ይህ ልዩነትና አንድነት የሚያስገድደው የፖለቲካ ዘይቤ

ይመስለኛል። ቅድም አያቶቻችን እንደ ምእራባውያን በጭካኔ በእሳትና ብረት እየቀጠቀጡ ያዋደዱት ሳይሆን፣ ለሃገራዊ አንድነት በጋራ ባፈሰሱት የነፃነት ደምና በጋራ ድህነትና ደዌ ባለቀሱት እንባና ሰቆቃ ተቦክቶ የተለሰነ ሃገራዊ አንድነት በመሆኑ፣ በስሱነት ልንይዘውና ልንንከባከበው ያሻል እላለሁ።

ኤድዋርድ ጊበን እንዳለው አለሙን ረስተነው በአለሙም ተረስተን ለዘመናት ከባጀን በሁዋላ፣ ድንገት ብንን ስንል፣ እጅግ ብዙ ርቀው ስለጠበቁን፣ ከአውሮፓውያኑ ለመድረስ "ፈጣኑ መንገድ እኔ የያዝኩት ብቻ ነው" በሚል፣ ሁላችንም ጉጉታችንና ረሃባችን ባስገደደን መንገድ መኳዝን ስለመረጥን፣ ብዙ የአቋራጭ መንገዶችን ስናሰላስልና ስንሯሯጥ፣ ጊዜ አግኝተን ለመደማመጥ ባለመቻላችን፣ ዛሬ ከ99 የማያንሱ ፓርቲዎቸ ቀፍቅፈን እንገኛለን። በአለሙ የታዩ የፖለቲካ ዝንባሌዎች ሁሉ ማራጋፍያ የሆንን ይመስል፣ ከህገ መንግስታዊ ዘውደኛ እስከ ወያኔያዊ ሃገር አውዳሚ ሃይል ድረስ፣ በየመስኩ የተሰለፈው ኢትዮጵያዊ የትዬለሌ ነው። አንድ ጓደኛዬ ሲቀልድ ከምንለብሳቸው ሳልቫጅ ልብሶች ጋር አብረው የሚመጡት የቀድሞ ባለቤቶቻቸው ቆሌዎች እየሰፈሩብን፣ ከአውሮፓ እስከ አውስትራሊያ ከኢንዶኔዥያ እስከ ደቡብ አሜሪካ ያንቀዠቅዡናል እያለ ያሾፋል። በትምህርት ስርአታችንም፣ ከአሜሪካ የሰላም ጓዶች እስከ ህንድ መምህራን የተቀየጥን፣ በከፍተኛ ትምህርት ተልእኳችንም፣ ከምእራብ ጀርመን እስከ ኪዩባ ህዝባዊ አብዮት እጅግ በተለያዩ ባህሎችና ርእዮተአለሞች የተጠመቀ የተማረ ሃይል ያፈራች ሃገር በመሆኗና፣ እንደ ጃፓናውያን አንድ በሚያደርገን ሃገራዊ ትውፊትና ልማድ የታሰረ ምሁር ባለመሆኑ፣ ኢትዮጵያንም የምናይበት አይን እንደ ስልጠናችን ዝብርቅርቁ የወጣ ነው ማለት ማጋነን አይመስለኝም። እንዲህ የተቀየጠ ምሁራዊ ሃይል፣ በተለይ በመጀመሪያው ዴሞክራሲያዊ ርምጃ (መድረክ) ወቅት፣ ተፅእኖው ከፍተኛ ስለሆነ፣ ሁሉም የአቅሙን ወርውሮና ተንፍሶ እፎይ የሚልበት የጋራ መድረክ ካልተመሰረተ፣ ችግራችን በጥቂት ድርጅቶች ወይም መሪዎች "አውቅልሃለሁ" ባይነት ሊፈታ የሚችል ነው ብሎ አቃልሎ ማየት ግብዝነት ይመስለኛል። ይህ ሌላው የህብረት ትግልን የግድ የሚያደርገው ምክንያት ይመስለኛል።

የምሁራዊው ሃይሉ እንደ ስልጠናውና እንደ ርእዮተአለሙ ዝብርቅርቅ ከመሆኑ ባሻገርም፣ ባለፉት አራት አሰርተ አመታት፣ አገዛዝን በመቃወም በተደረጉት ትግሎች የተሳተፈው ሃይል እጅግ ብዙ ሆኖ ሳለ፣ በተሰለፈባቸው ድርጅቶችና ርእዬቶች ሽንፈት ሲገጥመው፣ በአለሙ ለመበተን ተገዶ አዲስ "የዳያስፖራ" ማህበረሰብ በመመስረቱና፣ ከአዲስነቱም በመነጨ ከታደጉት ሃገሮችና ህዝቦች ቋንቋና ባህል ጋር እስኪላመድ ድረስ አድካሚና ግር የሚልም ስለሆነበት፣ ይህ የትግል ልምድ ያለው ሃይል የግል ኑሮውን ለማሸነፍ እጅግ ተበታትኖ ይታያል። እንደ ኮሪያዊያኑ፣ እንደ ቻይናውያኑ ጠንካራ ማህበረሰቦችን ገና አልመሰረተም። ከዚህ መበታተኑም በመነጨ በሃገሩ ለሚደረጉት የፖለቲካ ትግሎች፣ አስተማማኝ ደንደስ ሊሆን አልቻለም። በዚህ ላይ የሚሰጠው ውሱን ድጋፍም በብዙ ትናንሽ ድርጅቶች ዙሪያ የተከፋፈለ በመሆኑ፣ አመርቂ ድጋፍ ማድረግም አልተቻለውም። የፖለቲካ ትግሉ መተባበር፣ ይህን የተባበተነ ትግል በማሰባሰብ፣ ትልቅ የአቅም ግንባታ ለማድረግ ያስችለዋል ብዬ አስባለሁ።

በሶስተኛ ደረጃ፣ ወያኔ አጀንዳው ያደረገው የብሄረሰቦች ጉዳይ፣ የወያኔ የግል ጉዳይ ይመስል የተተወ በመሆኑና፣ አልፎ አልፎም የብሄረሰቦችን መብት ያነሳ ሁሉ እንደ ፀረ አንድነት እየታየ የተወገዘባቸው ሁኔታዎች፣ (በተለይ በዳያስፖራው ማህበረሰብ ጪሂ መገናኛ ብዙሃን) ብዙ ስለነበሩ፣ ወያኔ በዘውግ ለመከፋፈልና እድሜውንም ለማራዘም እንዲችል በር ተከፍቶለታል። ኦነግን እየመነጠርኩ ነው በሚል ሽፋን በኦሮሞው ህዝብ ላይ እልቂትን ያወርድ የነበረው ወያኔ፣ ቀስ ብሎ የኦጋዴን አርነት ግንባርን በመዋጋት ስም በኢትዮጵያውያን ሱማሌ ወገኖቻችን ላይ ግፍና አበሳን ሲያወርድ ከርሞ ነበር። አሁን ደግሞ፣ የመንግስት ግልበጣ ሙከራ ተደረገብኝ በሚል ከለላ፣ የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አባላትን እመነጥራለሁ  በሚል ቀቢፀ ተስፋ፣

በአማራው ህዝብ ላይ ከፍተኛ ብካይ በማድረስ ላይ ይገኛል። ነገ ደግሞ “አረና ትግራይን” የአማራ ቡችሎች ብሎ፣ በመቀሌ ሃውዜንና አዲግራት የአፈና ርምጃ ቢጀምር ከቶ ሊገርመን አይችልም። ከነዚህ ሁሉ የወያኔ በትሮች የተማርነው ነገር ቢኖር ግን፣ ወያኔ በስልጣኑ እስከመጡበት ድረስ ለማንም የማይመለስ መሆኑንና፣ በተናጠል በየተራ ከምንመተር፣ የጋራ ጉልበታችንን አስተባብረን የጋራ ጠላታችንን መመከት አማራጭ የሌለው መሆኑን፣ የ18 አመታት እንግልታችን ሁላችንንም ያስተማረበት ወቅት ላይ መድረሳችን ነው።

የህብረት ትግልን አስፈላጊነት ብዙዎቹ ድርጅቶችና አመራሮቻቸው የተረዱበት ወቅት ላይ ደርሰናል የሚል እምነት አለን። ስለሆነም የብሄረሰቦች ጉዳይ ለወያኔ የስልጣን ገበጣ መጫወቻ የሚተው ሳይሆን፣ አጀንዳውን ከወያኔ ቀምተን፣ አላማችን አድርገን የተነሳነው የዜጎች ነፃነት ታላቅ ህልም፣ የወል ጥያቄ የሚያነሱ ዜጎችን መብት ሳያስከብር፣ ካለመበት መድረስ እንዳይቻለው አውቀን፣ በየዋህነት ወደጎን ገሸሽ የተደረገውን የብሄረሰቦች ጉዳይ የሚመለከተን መሆኑን አስምረንበት፣ ከኦነግ የተለያዩ ሃይሎችም ጋር ሆነ፣ በወያኔ አፍንጫ ስር “ወጊድ ለወያኔ ዘረኝነት” ብለው የሚረባረቡ ሌሎች ሀይሎቸን አጋርነታቸንን በማሳየት ብርቱ ልንላቸው ይገባል።

በአራተኛ ደረጃ፣ ግንቦት ሰባት ይዞት የተነሳው ውሱን አላማ፣ ይሄውም የሃገሪቷን አንድነት አስጠብቆ ከዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር የምትደርስበትን ሁኔታ ማመቻቸት ግብ፣ ሁሉንም የፖለቲካ ሃይሎች ያካተተን የሽግግር መድረክ ያለመ በመሆኑ፣ ወደዚያም መድረሻው ድልድዩ ሃገራዊ አንድነትንና ዴሞክራሲን የሚሹ ሃይሎችን ሁሉ በጋራ ያስተባበረ ትግልን በማጧጧፍ በመሆኑ፣ ከግባችን ለመድረስ ከህብረት ትግል ውጪ የሚቻል አይደለም። በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የህብረት ትግል እጅግ ተመራጭ ነው። ግን እስከዛሬ ለምን መተባበር ሳይቻለን ቀረ?

<u>የህብረት ትግል ሙከራዎች ያገጠሙት እክሎች ምን ነበሩ?</u>

ይህን ርዕስ ሙከራዎቹን ያደረጉት ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ቢናገሩት የሚቀልም ሆነ ይበልጥ ተገቢ ይመስለኛል። ከራሱ ከኢህአዴግ ጀምሮ ብዙ የህብረት ትግል ሙከራዎች ተደርገዋል። በደርጉ ዘመንም ኢጭአት፣ ኢማሌድህ ወዘተ የተሰኙ የገዢው ሃይል የህብረት ሙከራዎች እንደነበሩ አይዘነጋም። ኢማሌድህ በድርጅቶች ህብረት ተጀምሮ፣ በሂደት አንድ የኮሙኒስት ፓርቲ እንመሰርታለን ተብሎ፣ በመጨረሻ ገኖ የወጣው የመንግስቱ ሃይለማርያም ወታደራዊ ቡድን፣ ሰደድ፣ “በቆራጡ መሪያችን ዙሪያ ካልሆነ፣ በድርጅቶች ህብረት ፓርቲ መመስረት አይቻልም” ወደሚል ጅልነት ተሸጋገረ።

ደርጉ ወታደራዊ ጡንቹ ፈርጥሞ ኢዲዩንም ኢህአፓንም ካዳከማቸው በሁዋላ፣ የዛሬ 25 አመታት ገደማ፣ ከአንፃራዊ የሃይል ደካማነታቸው በመነሳት፣ ሃይላቸውን ለማስተባበር በማሰብ፣ ኢዲዩና ኢህአፓ በሊበራል አስተሳሰብ ዙሪያ የተስማማ የጋራ ግንባር አውጀው ነበር ። ሆኖም በመርህ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ደካማ ጉልበትን ለማሰባሰብ የተደረገ ሙከራ ስለነበር፣ ከዛሬ 18 አመታት በፊት ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ፣ ህብረቱ ሊፈርስ ችሏል።

ወያኔ ስልጣን ከያዘ በሁዋላ በኢህአፓ ግንባር ቀደምትነትና በመኢሶን ተባባሪነት በዳያስፖራና፣ ከሃገር በቀል ብሄርተኛ ፓርቲዎች ጋርም በመዳበል የተሞከሩ ብዙ የህብረት ጅምሮች ነበሩ። እንደሚታወቀው ኢህአፓና መኢሶን አናርኪስትና ባንዳ ተባብለው በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ ደም የተቃቡ ድርጅቶች ነበሩ። የዚህን የታሪካቸውን ቁርሾ፣ መሪዎቹ ምን ያህል ቁጭ ብለው ተወያይተውና የጋራ መተማመን ላይ ደርሰው፤ ከዚህም ውይይት ጠንካራ የአመለካከትና የስነልቡና አንድነት ፈጥረው ሕብረቱን እንደፈጠሩ አላውቅም። እኔ ስገምተው ወያኔን ከስልጣን ለማሽቀንጠር ብቻ የተደረጉ ስምምነቶች ብቻ ስለነበሩ፣ በዚህም ምክንያት እርስ በእርስ የመጠባበቅ፣ ያለሙተማመን፣ የመሻኮትና የመጠላለፍ ብሎም የመተማማት ችግሮችን በውስጡ

አዝሎ የሚካሄድ ህብረት ስለነበር ይሆን እንዴ ዘላቂነት ያጣው የሚል ጥርጣሬ በብዙ ሰው አእምሮ ውስጥ ሳይቀረፅ አይቀርም እላለሁ። ቢያንስ ግን በኔ ግምት እንዲህ አይነት ታሪካዊ ጠባሳን ለአገራዊ ጉዳይ በሚል ተሻግሮ መሄዱ የሚያስመሰግነውን ያክል የታሪኩን ጉዳይ ቢያንስ መሪዎቹ ተነጋግረውበትና አንድ አይነት መግባባት ላይ ደርሰውበት፤ አባሎቻቸውንም አሳምነውበት ቢሆን ሕብረቱን ለማዝለቅ ይጠቅም ይሆን እንዴ የሚል ጥያቄ ይጭርብኛል። ትምህርት የምንቀስምበት ተመክሮ መሆኑም ይሰማኛል።

ሌላው የግንቦት 97 ምርጫ ከመምጣቱ በፊት በሃገርቤት ውስጥ የተሞከረው የቅንጅት የተባበረ ትግል ነው። በ1992 በተካሄዱት የከባቢና ፌዴራላዊ ምርጫዎች፣ ተቃዋሚዎች እርስ በርሳቸው ባይጠላለፉ ኖሮ ቢያንስ አዲስ አበባን ለማሸነፍ ይችሉ ነበር የሚል ግምገማ የነበራቸው ሰዎች፣ በ1997ም ያ እንዳይደገም አንድ ነገር ማድረግ አለብን በሚል የቅንጅትን መፈጠር እውን እንዲሆን ማድረግ ችለው ነበር። እንደታለመውም አራቱን  ድርጅቶች በማስተባበር፣ ከአዲስ አበባም አልፎ በሃገር አቀፍ ደረጃም ምርጫውን ማሸነፍ የተቻለበትንም ሁኔታ መፍጠር ተችሎ ነበር። ያ ለውሱን አላማ፣ ምርጫውን ለማሸነፍ የተመሰረት የትግል ህብረት ግን፣ ወደ ላቀ ሕብረት ለመመስረት ሲሸጋገርና፣ በወያኔ በኩል የሚመጣውን የተቀናበረ ጥቃት ለመመከት የሚያስችል የአመለካከትና የአመራር ጥንካሬ ከማዳበሩ በፊት ተጠቃ። አንድ ሆኖ መቀጠልም አልሆነለትም። ይብስ ብሎም ዋናውን ጠላቱን ትቶ ለረጅም ጊዜ የሚያሳፍር የእርስ በእርስ ንትርክ ውስጥ ገብቶ አረፈው። ይህ ክስተት ወደፊት ለሚያጋጥመን ሁኔታ ብዙ ሊያስተምረን የሚችል ትምህርት ይገኝበት ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

## ከተሞከሩት የህብረት ትግሎች ምን እንማራለን?

ዋነኛው ትምህርት የህብረቱን ግብ ግልፅ አድርጎ ማስቀመጥ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይመስለኛል። የኢትዮጵያ አንድነትና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ግባችን ሊሆን ይገባል በሚል ግንቦት ሰባት ንቅናቄ በግልፅ ያስቀመጠው አላማ አለ። ይህንን ግብ አላማቸው ያደረጉ ህብረ ብሄራዊም ሆኑ ብሄራዊ ድርጅቶችን፣ በሃገር ቤቱ የትግል አውድማ ተጨባጭ ስራን የሚሰሩ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ የህብረቱ አባል መሆን ይገባቸዋል እላለሁ። እነኝህ ሁለት አላማዎች ወሳኝ ናቸው ስንልና የሕብረቱ አባል ለመሆን አስፈላጊ ናቸው ስንል በጉዳዩ ዙሪያ ምንም ክርክር አይነሳም ለማለት አይደለም።

የመጀመሪያውን ግብ በሚመለከት ነገሩን በጥርጣሬ የሚያዩና በተለይ የዴሞክራሲው ሙከራ እክል ቢገጥመው ‹ከኢትዮጵያ ውጭ ሰላምና ዴሞክራሲን ለመፈለግ እንዳንሞክር መንገዱ ከአሁኑ ለምን ይዘጋል? ‹የመገንጠል መብት መኖር በዴሞክራሲው ላይ መተማመን እስከሚፈጠር ድርስ ማስተማመኛ አይሆንም ወይ? ኢዴሞክራሲያዊው ወያኔ እንኩዋን ይህን መብት በሕገመንግስቱ ውስጥ አስገብቶት የለም ወይ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ለምን ይፈሩታል? የሚሉ ጥያቄዎች በተለይ በዘውግ ከተደራጁ ድርጅቶች እንደሚነሳ አውቃለሁ። ይህንን በሚመለከት ከሁለቱም ወገን ብዙ መከራከሪያዎች መቅረብ የሚችሉ ቢሆንም ፍርሀቱን ይቀርፍ እንደሆን ለጊዜው ሁለት መከራከሪያ ላቅርብ። የመጀመሪያው መከራከሪያ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታን አስቸጋሪነት የሚመለከት ነው። እንኩዋን በግማሽ ልብ ገብተንበት በሙሉ ልባችን ገብተንበትም ብዙ እክሎችን አልፈን የምንደርስበት ስርአት ነው። ከተመሰረተ በሁዋላ ጠንካራ የሆነውን ያክል በእንደኛ አይነት አገር ለመመስረት ቢያንስ በፖለቲካ ልሂቁ ዘንድ በግለሰቦች መሪዎች ወይንም ድርጅቶች ላይ ሳይሆን በጨዋታ ሕጉ ላይ ጠንካራና የማይዛነፍ ስምምነት ይፈልጋል። ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቁዋማት የሚገነቡት በልሂቆች መሀከል ከፍተኛ የፖለቲካ ሽኩቻ ሲኖርና በጫወታው ሕግ ዙሪያ ግን የሽኩቻውን ያክል የጠነከረ ስምምነትና ታማኝነት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ይህ የሚፈጠረው ደግሞ ጨዋታው ለሚካሄድበት የፖለቲካ ማህበረሰብ ጠንካራ ታማኝነት ሲኖር

ነው፡፡ በምርጫ የተሸነፈ ወይንም የሚፈልገውን የፖለቲካ ስልጣን ያላገኛ ብሄረተኛ ነኝ ባይ ንኡስ ከበርቴ ሁሉ በፈለገ ጊዜ ጥቂት የሚጮሁ ተከታዮቹን ይዞ፤ የፖለቲካ ስርአቱን የሚያግትበት ሁኔታ የሚፈጠር ከሆነ እራሱን ከምር የሚወስድና ለጫወታው ህግ ክብር ያለው የዴሞክራሲ ስርአት ለመገንባት በፍፁም ከባድ ነው የሚሆነው፡፡ በሌላ በኩል ግን እስታሊናዊ የሆኑ የወያኔ አይነት መንግስቶች ይህንን አይነት ‹መብትን› ሕገ መንግስት ላይ ለመፃፍ የሚደፍሩትና በዚህም የበለጠ ዴሞክራቶች ነን ብለው የማያውቃቸውን ለማሞኘት የሚሞክሩት፤ የራሳቸውን ሕገ መንግስትም ከምር ስለማይወስዱት ነው፡፡ ለነሱ ሁሉም ነገር ጊዜያዊ የመግዢያ መሳሪያ ነው፡፡ ሕግ ራሱ የማጥቂያ መሳሪያ ነው፡፡ ለነሱ ሕግ ማለት የተፃፈውና ሁሉም የሚያውቀው ሳይሆን እነሱ የሚፈልጉትን ነገር የሚያደርጉበት ነው፡፡ የሚከበር ነገር የለም፡፡ ወያኔ የመገንጠል መብትን አይደለም (ምናልባት አስፈላጊ ከሆነ ለራሱ ሊጠቀምበት ሲፈልግ ካልሆነ በስተቀር) ፤ እንዲሁ እራስን በመረጡት የአካባቢ ሰው ለማስተዳደር የማይፈቅድ፤ በስም ደረጃ እራስን የማስተዳደር መብት ሰጥቶ ግን መሪዎቹን እሱ ለማስቀመጥ ምንም አይኑን የማያሽ፤ ከዚያም አልፎ ያንን ሕዝብ የሚወክለውን ድርጅት እሱ ራሱ ያስቀመጠው ካልሆነ ምንም የማያምን መንግስት መሆኑን፤ ይህ መስሎአቸው በአንድ ጊዜ ለሙከራም ቢሆን ተጠግተውት የነበሩት የዘውጌ ማህበረሰብ ድርጅቶች በሙሉ የሚያውቁት ነው። ማናቸውም መብቶች የሚከበሩት ለመብት ክብር ያለው ስርአት ሲኖር ነው። ለነኝህ መብቶች ከልቡ የሚቆረቆር አካል ከልቡ መስራት ያለበት የሰውን መብት ከልቡ የሚያከብር ስርአት ለማቆም፤ ይህን ስርአት ከልባቸው ለማቆም ከሚፈልጉ ሀይሎች ጋር ሆኖ መታገልና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን በአገራችን መገንባት ነው። ከዚህ ውጪ የሚመጣ ምንም ጥቅም ወይንም የሚከበር ምንም መብት አይኖርም። ይህንን ከልባችን ስለምናምን ነው በጣም ግልፅ ሆነን ይህን ስርአት በዚህ የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ በጋራ ለመገንባት የቆረጡ ሀይሎች እንዲህ አይነቱን በመርህ ላይ የተመሰረተ ትብብር መመስረት አለባቸው የምንለው።

ሌላው ከእስከ ዛሬዎቹ የህብረት ሙከራዎች የተማርነው፣ ህብረት ድርጅት ነኝ ያለ ሁሉ የሚገባበት ሳይሆን ድርጅት መሆኑን ከሚገልፀው ስሙና ፕሮግራሙ በላይ በተጨባጭ፤ በተግባር በትግሉ ሜዳ ላይ ለትግሉ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ በሚችሉ፤ ትግሉን ከምር በሚወስዱ ሀይሎች መሀከል የሚፈጠር የምድር ላይ ግንባር መሆን አለበት። እራሴ የምመራውና እንደፈለግሁ የማደርገው ሶስት ሰው ያለበት ድርጅትም ቢሆን እመሰርታለሁ እንጂ በአላማ ከሚስማሙኝ ድርጅቶች ጋር ተቀላቅዬ እንዴት እሰራለሁ ብሎ የሚያምን ግብዝ ሁሉ፤ ወይንም ሌላው ኑሮ ሰልችቶኛል በማህበረሰቡ የሚያሳውቀኝ የፖለቲካ ሱቅ መክፈት አለብኝ ብሎ የሚያምን ሁሉ ፓርቲ መስርቼአለሁ እያለ፣ ራሱን እንቅልፍ ነስቶ ሌላውንም የሚያምስበት የፖለቲካ አካሄድ ሊቆም ይገባዋል ብለን እናምናለን። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እራሳችንን ከኛ ለተሻለ መሪ፤ ድርጅታችንን ከኛ ድርጅት ለላቀና ውጤት ለሚያመጣ ሰፊ ድርጅት፤ በግላችን አጠንክረን ከምናምንበት ግን ተግባራዊ ሊሆን ከማይችል እምነታችን ይልቅ ከሌሎች ጋር አስተሳስሮ ሊያታግሉን ለሚችሉ መለስተኛ እምነቶቻችን ለመልቀቅ በመርህ ደረጃ ፈቃደኛ ሳንሆን ከራሳችን በላይ ለሆነ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ አላማ እንገዛለን ማለት ዘበት ነው። ለዚህም ነው፣ <<በሃገር ቤቱ የትግል አውድማ ተጨባጭ ስራን የሚሰሩ>> የሚል መመዘኛ ማስገባት አስፈላጊ የሆነው። ለትግሉ ከውጭ ሆነው አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚፈልጉ የተለያዩ ቡድኖች ወይንም ግለሰቦች ሊኖሩ አይገባም ለማለት አይደለም። ይገባልም ለትግሉም በጣም ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። የሚፈጠረው ግንባር ተጨባጭ የምድር ላይ ስራ እንዲሰራ ከሆነ የሚመሰረተው ግን ይህን ለማድረግ በተዘጋጁ ሀይሎች መሀል መሆኑ የግድ ነው። አባል ድርጅት አድርጎ ሊያቅፋቸው የሚገባውና ትክክልም የሚሆነው ይኸው ነው።

የከዚህ በፊት ልምዳችን ይህን ማድረግ ያልቻለው በሁለት ምክንያት ይመስለኛል፡፡ አንደኛው የሚፈጠሩ ትብብሮችንና ተግባራዊ ግንባሮችን መለየት ላይ የሚፈጠር ብዥታ ይመስለኛል፡፡

የፖለቲካ ድርጅት ያልሆኑ (ለምሳሌ የሙያ ድርጅቶች፤ የሰብአዊ መብት ተሙዋጋች ቡድኖች…ወዘተ) ሁሉ የሚሰባሰቡበት በተወሰኑ ቁልፍ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚደረግ አገራዊና በተወሰነ ደረጃም ጊዜያዊ ትብብር (ለምሳሌ ሰብአዊ መብት እንዲከበር፤ የታሰሩ የህሊና እስረኞች እንዲፈቱ…ወዘተ) ሊፈጠር ይችላል። ትክክልም ነው። ይህ ግን እኛ ከጠራነውና የጋራ ትግሉን ወጥ አመራር ሰጥቶና ሁለገብ ትግል አድርጎ እዳር ለማድረስ ከሚመሰረት ግንባር ጋር ይለያል። እኛ የጠራነው በምድር ላይ ሆነው ትግሉን ለማድረግ በወሰኑና ለዚህም በተደራጁ ሀይሎች መሀከል ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። ይህ ማለት ከሌሎች በውጭ ብቻ ከተቁዋቁዋሙ ሀይሎች ጋር በተወሰኑ ስራዎች ላይ አይተባበርም ማለት አይደለም። ሁለተኛው ምክንያት ግን የሚመስለው ዝም ብሎ ይሉኝታ ነው። የፖለቲካ ድርጅት ነኝ ያለ ሁሉ ለምን አይገባም፤ ይህ ማግለል ይመስላል፤ ጥቂት ግለሰቦችም ቢሆኑ እነሱን ከማስቀየም ዝም ብሎ ማስገባት ይሻላል፡ ካልገቡ ከዳር ሆነው ይበጠብጣሉ…ወዘተ በሚል የሚደረግ ሀቀኛ ያልሆነ የይሉኝታ አካሄድ ነው። የዚህ ችግር ደግሞ ቀድሞውንም በቅንነት ስላልተደረገ ብዙም ሳይቆይ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሀሜት አለመተማመንና አለመከባበር፤ ይፈጠርና ትብብሩን ይበክለዋል፤ ያዳክመዋል። ትግሉ የሚፈልገው ቆራጥነት ሳይኖር፤ በጋራ መስዋእትነት ለመክፈል በመፍቀድ ላይ የተሳሰረ መተማመን ከሌለ ደግሞ ዘላቂ ትብብር ወይንም ግንባር ሊመሰረት አይቻልም።

ሶስተኛው ትምህርት፣ በወያኔ ባላንጣነት ላይ የማይደራደር የትግል ግንባር ሊሆን ይገባዋል። ከእንግዲህ ወያኔ የህዝብ ጎራን መቀላቀል የሚችለው፣ ራሱን ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተገዢ ለማድረግ ሲወስንና፣ ኢትዮጵያ የምትባል በአያቶቻችን መስዋእትነት የተገነባች ለሁላችንም እኩል የሆነች አንድ ሃገር መኖሯንና፣ አንድነቷም ለድርድር የማይቀርብ መሆኑን ወዶም ሆነ ተገዶ ሲቀበል ብቻ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። የሚፈጠረው ግንባር እንደዚሁ ጊዜያዊ ማስፈራሪያ ለመሆንና ጊዜ ጠብቆ በወያኔ ትናንሽ መደለያዎች እጁን ሰጥቶ ጠቅልሎ የሚገባ ሊሆን አይገባም። የዚህ አይነቱን ግንባር ከመፍጠር አለመፍጠሩ ይሻላል። ለዚህ ነው በመርህ ላይ የተመሰረተ፤ የሚሄድበትን የሚያውቅና ወጥ አመራር ያለው፤ እዚያም እንዴት እንደሚደርስ በደንብ ያሰበበትና እዚያ ለመድረስ በሚያስፈልገው እስትራቴጂም ላይ ሙሉ ስምምነት ያለው ትብብር መሆን የሚገባው።

አራተኛው ትምህርት፣ አንዳንድ ጉዳዮች በይደር ቢቀመጡ፣ ዛሬ ትኩረት ልናደርግባቸው በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ እንድናተኩር ስለሚያደርገን፣ በሆነው ባልሆነው ከመናቆር ይጠብቀን ይመስለኛል። ለሁሉም ችግሮች ዛሬ መልስ ሊኖረን አይገባም። ሃገራችን ባለችበት ሁኔታ የሚያስፈልጋት፣ የተለያዩ ማህበረሰቦችን ጥቅም ወክለው የሚደራደሩ ፖለቲከኞችን ሳይሆን፣ “በየዋህነት ሸማ የተጋረዱ” (ጆን ሮውልስ ‹ቬይል ኦፍ ኢግኖራንስ›፤ የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ታሳቢ ያደርጋል) አርቆ አሳቢ ሃገር ወዳዶችን ነው። የኦሮሞውን፣ የሙስሊሙን፣ የሴቶችን ወዘተ ጥቅም እንዴት ባለአቋም ላስከብር ብለው በሚያውጠነጥኑ ፖለቲከኞች ድርድር ሳይሆን፣ ዛሬ ሃገራችን ካለችበት መቀመቅ እንዴት ትውጣ፣ ለሁሉም ዜጎቿ ፍትሃዊ የሆነ ስርአት መሰረት እንዴት እንጣል የሚሉ አርቆ ተጨናቂዎች የተሰባሰቡበት የትግል ግንባር ቢሆን፣ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መስራች አባቶችና እናቶች ሸንጎ ጅማሮ ሊሆን ይችላል፣ ይገባልም ብዬ አስባለሁ። አለበለዚያ ዝርዝር የፖለቲካ ፕሮግራሞችን ይዘን ለመደራደር ብንሞክር፣ “እርሷ መሬት የግል ይሁን ያለችው ገንዘብ ያላቸው ትግሬዎችና ጉራጌዎች ከደሃው ኦሮሞ ላይ ገዝተው ህዝባችንን መሬት አልባ ልታስደርግ አስባ መሆን አለበት” ወዘተ የሚል ተቃውሞና የማያልቅ ክርክር ስለሚጋብዝ፣ ዝርዝር የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ፕሮግራሞች፣ ከሽግግሩ ዘመን በሁዋላ ለሚደረግ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ መተው ያለበት ይመስለኛል። ስለቀሰምናቸው ትምህርቶች ይህን ካልኩ ዘንዳ፣ በመግቢያዬ እንዳልኩት በናንተም ተሳትፎ እንዲዳብር፣ ዝርዝር ውስጥ ከመግባት ልቆጠብና፣ ወደ ህብረቱ የመርህ መሰረቶች ላምራ።

## የህብረት ትግሉ በምን አይነት መርህ ላይ ይገንባ?

ከላይ በቁጥር ሶስት ካነሳሁት ጉዳይ ጋር በተሳሰረ፣ "ዛሬ ሃገራችን ካለችበት መቀመቅ እንዴት ትውጣ፣ ለሁሉም ዜጎቿ ፍትሃዊ የሆነ ስርአት መሰረት እንዴት እንጣል የሚሉ አርቆ ተጨናቂዎች የተሰባሰቡበት የትግል ግንባር ቢሆን" እንደሚጠቅም አውስቼ ነበር። ይህ ከህብረቱ መሰረታዊ መርህ ጋር የተሳሰረ ጉዳይ ይመስለኛል። በሃገር ቤትም ሆነ በዳያስፖራ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ። ብዙ ኢትዮጵያውያን ለለውጥ ይደክማሉ። ሆኖም ድካማቸው እስካሁን ፍሬ አልሰጠም። አንዱ ችግር መስሎ የሚታየኝ፣ ከነበረንና ካለፍንበት የፖለቲካ ልምድ አኩዋያ በድርጅቶች ውስጥ የሚነሱ ልዩነቶችን ለመፍታትም ሆነ፤ የድርጅቶችን ሕልውና አደጋ ላይ ሳይጥል የድርጅት አመራርን ግልፅና ወጥነት ባለው ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ለመለዋወጥ የሚያስችል የውስጥ ድርጅት ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ልምድ አላዳበርንም። ወያኔን በአመለካከትም ሆነ በአደረጃጀት በልጠን ልናሸንፈው የምንችለው ከሱ የተሻለና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ የሆነ አደረጃጀት ሲኖረን መሆኑ ሊሰመርበት ይገባዋል።

ሁለተኛው የመርህ ጥያቄ ለኢትዮጵያችን ያለን ርዕይ የተደላደለ ዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ምስረታን ያለመ ሊሆን ይገበዋል። በዝርዝር ፕሮግራም ደረጃ ሳይሆን፣ በፍልስፍና ደረጃ ለተደላደለ ዴሞክራሲያዊ ህብረተሰብ መሰረት የሚሆኑትን እሴቶች አሽቶና አበጥሮ፣ ምርቱን ከግርዱ ለይቶ፣ የህብረት ትግሉን መንፈስና ቀልብ የሚገዙ አጠቃላይ መርሆዎች ማድረግ ተገቢ ይመስለኛል። ይህን ስል ምን ማለቴ ነው? የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ መሰረታዊ መዋቅር ምን ሊሆን እንደሚገባው ስምምነት ላይ መድረስ አለብን ማለቴ ነው። ይህም ማለት የተደላደለና የተዋጣለት ህገመንግስታዊ ስርአት የሚቆምባቸው ዋልታዎች (ምሶሶዎች) ምን እንደሆኑ መለየትና፣ ለነዚህም ግብራዊነት መረባረብ ነው። እነዚህ ምሶሶዎች ምንድን ናቸው? አንዱን ምሶሶ ብቻ ላካፍላችሁ።

የሰመረ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ለማቆም፣ እጅግ ወሳኙ ጉዳይ፣ የተጨባጩን አለም ውሱን ድንበሮች ጥሶ፣ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የገጠጠ ሃቅ ርቆና ንቆ፣ በምናባዊ ሃይል ወደሳሉት ዴሞክራሲያዊ ዕፁብነት (ፐርፌክሽን) ለመድረስ ለመንፏቀቅ፣ ለማቃተት፣ ለመዳህ ብሎም ለመሮጥ በቁርጠኝነት መወሰን ነው። ሰው በተፈጥሮው ሽቅብ ወደአርያም ለመወንጨፍ የሚያስችሉት አክናፋት ያሉት ቅድስናና በጎነት በውስጡ የሰነቀ ፍጡር ነው ከሚል ብሩሃዊ አመለካከት የሚነሳ ሃሳብ ነው ይሄኛው። በአምክህዮታዊ ሃይል የደረሱበትን ይህን ዴሞክራሲያዊ ዕፁብ ኢላማ፣ ባዶ ቅዠት ሳይሆን፣ ሊደረስበት የሚችል መሆኑን ከልብ መቀበልና፣ መንገዱ አባጣና ጎርባጣ ቢበዛበትም አዎን ይቻላል! በሚል ፅናት ጉዞውን መጀመር ያስፈልጋል። በዚህ ላይ ከተስማማን፣ የጦርነቱ ግማሽ ተገባዷል ማለት ነው። በአጠቃላይ ስለ ሰው፣ በተጨባጭም ስለ ኢትዮጵያውያን ማንነት እንዲህ አይነት ዕምነት ከሰነቅን፣ የህብረት ትግሉ ሊያስጠነቅራቸው ወደሚገባቸው አጠቃላይ የፖለቲካ ግንዛቤዎች ያለ ብዙ ውጣ ውረድ ያሸጋግረናል። ከነዚህም ውስጥ ዋነኛ የሚመስለኝ፣ ስለወደፊቱ ኢትዮጵያ ህብረተሰብ የሚኖረንን ግንዛቤ ያስጨብጠን ይመስለኛል። *ይህም ግንዛቤ፣ መፃኢው የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ነፃና እኩል በሆኑ ሰዎች (ዜጎች) መሃል በሚደረግ ሚዛናዊ (ርቱአዊ) ትብብር ላይ የተመሰረተ ይሆናል የሚል ጭብጥ ላይ የተመሰረተ ይሆናል*። ይህም ርቱአዊ ትብብር ሌላ ሳይሆን በነፃና እኩል አባላት መሃል በተደረሰ የጋራ ስምምነት፣ የጋራ ጥቅማችንን ያስከብራል ብለው ተደራድረው በደረሱባቸው አንቀፆች የታሰረ ይሆናል። በመድበለ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች ለታጠረችው ኢትዮጵያችን ደግሞ፣ ለዜጎች ሁሉ ተቀባይነት ያለው፣ ከጋራ ስምምነታቸው ባመነጩት ስርአት ከመተዳደር የተሻለ የተደላደለ ስርአት ሊኖር ከቶ አይችልም። ይህ ከረጅም ድርድር የወጣ ስርአት በባህሪው ፉንጋ፣ አንካሳ፣ አቅመ ቢስ መስሎ ሊታይ ይችላል። ሆኖም የየትኛውም ማህበረሰብ (ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣

ዘውግ፣ ሙያ ማህበር፣ ፓርቲ ወዘተ) የፈለገውን ሁሉ የሚያገኝበት ሳይሆን በሰጥቶ መቀበል የተደረሰበት፣ ለየትኛውም የማያደላ ሚዛናዊ ማእከል በመሆኑ፣ የተደላደለ ርቱአዊ ስርአት የማሰገኘት ችሎታው የላቀ ነው እላለሁ። ይህን በመሰለ ሆደ ሰፊነትና አርቆ አስተዋይነት ላይ የተመሰረተ የጋራ ትግል ዛሬ መጀመር ከቻልን የኢትዮጵያችን ተስፋ እጅግ ብሩሃዊ ይሆናል እላለሁ።

## ማጠቃለያ

ውድ ወገኖቼ! እንዲህ አይነት የትግል ግንባር ለመፍጠር ሁሉም ድርጅቶች ዝግጁ ላይሆኑ ይችላሉ። ከፊሉ ከድርድር ለምትወጣ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለመድከም ፈቃደኛ ላይሆን ይችላል። የግሉን የፖለቲካ አጀንዳ ግብራዊ ማድረግ የሚችል እየመሰለው፣ በተናጠል መጓዙን የሚመርጥ ሊኖር ይችላል። ገሚሱ፣ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ አሃድነት ለመቀበል እያንገሸገሸው አማራጭ ስትራተጂዎችን ለመቆዘም ይፈልግ ይሆናል። አንዳንዱ፣ ፖለቲካ በዳያስፖራ መድረኮች የሚታዩበት ተግባር እንጂ፣ በሃገርቤት ግንባር መውደቅ መነሳት እንዳለበት ላይቀበል ይችላል። በዚህ ሁሉ የተነሳ፣ በተቃዋሚነት የተሰለፈው ሁሉ አብሮ በአንድ ግንባር ይጠቃለላል ማለት አይደለም። የተዘጋጁና፣ የቆረጡ ብቻ ጊዜ ሳያጠፉ ወደተግባር መሸጋገር የሚጠበቅባቸው ወቅት ላይ ደርሰናል። ድጋፋችሁ እንደማይለየን ፅኑ እምነቴ ነው።

አመሰግናለሁ!